Waggaa 9ffaa ...................Lak. 12
፱ኛ ዓመት....................ቁጥር ፲፪
9th Year..........................No. 12

Finfinnee, Muddee 18/1995
ፊንፊኔ፤ ታህሳስ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

# MAGALATA OROMIYAA

# መገለተ ኦሮሚያ

# MEGELETA OROMIA

| Too'annaa Caffee Mootummaa Naannoo Oromiyaatiin Kan Bahe | በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ |
|---|---|
| Gatiin Tokkoo.......................8·53 | ያንዱ ዋጋ.......................3.00 |
| Lakk. S.Poostaa.......................101769 | የፖ.ሣ. ቁጥር .......................101769 |

QABEENTAA

Dambii lakk 29/1995

Dambii Hundeessaa Waajjira pirojektii Adaamaa........... Fuula 1

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፳፱/፲፱፻፺፭

የአዳማ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ........ገጽ ፩

## Dambii Lakk 29/1995

Hojiilee Waajjira Piroojektii Adaamaa Waajjira Raawwachiisaa Pirojektii Siidaa Waregamtoota fi Giddugaleessa Aadaa Oromoo waajjira tokko jalatti yoo hojjetame bu'aa akka qabu waan itti amanameef;

Kaayyoo kana raawwachuu dhaaf Qajeelfama lakk 1/1993 fi Dambii lakk 25/1994 tiin hojiilee qaamota lamaaf kenname walitti qabee kan hojjetu waajjira tokko dambiidhaan dhaabuun waan barbaachiseef;

Manni Maree Bulchiinsa Mootummaa Naannoo Oromiyaa Heera Mootummaa keewwata 55 (6) irratti hundaa'uudhaan Dambii kana baaseera.

1. *Mata Duree Gabaabaa*
   Dambiin kun "Dambii Hundeessaa Waajjira Piroojektii Adaamaa lakk. 29/1995" jedhamee waamamuu ni danda'a.

2. *Hundeefama fi itti Waamama*
   1. Waajjirri Piroojektii Adaamaa kana booda "Waajjira" jedhamee kan waamamu qaama seeruummaa qabu fi kan mataa isaa danda'e, Waajjira Mootummaa Naannoo Oromiyaa ta'ee Dambii kanaan hundeeffameera.
   2. Itti Waamamni waajjirichaa Mana Maree Bulchiinsa Mootummaa Naannoo Oromiyaatiif ta'a.

3. *Teessoo Olaanaa*
   Teessoon Waajjirichaa inni olaanaan Magaalaa finfinnee keessa ta'ee, damee Magaalaa Adaamaatti qabaachuu ni danda'a.

4. *Kaayyoo*
   Waajjirichi Kaayyoowwan arman gaditti ibsaman ni Qabaata:
   1. Qorannoo foyyeessa maastar pilaaniitiin guddinni fi misoomni Magaalaa Adaamaa ittiin hogganamu geggeessuu fi qopheessuu;

## ደንብ ቁ. ፳፱/፲፱፻፺፭
## የአዳማ ፕሮጀክት ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣ ደንብ

የአዳማ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና የሰማዕታት ሐውልት አስፈጻሚ እና የኦሮሞ የባሕል ማዕከል ጽ/ቤት ሥር ቢሠራ ውጤት እንዳለው ስለታመነበት፣

ይህን አላማ ለማከናወን በመመሪያ ቁ. ፩/፲፱፻፺፫ እና በደንብ ቁ. ፳፭/፲፱፻፺፬ ለሁለት አካል የተሰጠውን አጠቃልሎ የሚሰራ አንድ ጽ/ቤት በደንብ ማቋቋም ስላስፈለገ፣

የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፮) ላይ በመመስረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩ <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ ደንብ «የአዳማ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁ. ፳፱/፲፱፻፺፭» ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

፪ <u>መቋቋምና ተጠሪነት</u>
፩ የአዳማ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከዚህ በኋላ «ጽሕፈት ቤት» ተብሎ የሚጠራ ህጋዊ ሰውነት ያለውና ራሱን የቻለ፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
፪ የጽ/ቤቱ ተጠሪነት ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል።

፫ <u>ዋና አድራሻ</u>
የጸ/ቤቱ ዋና አድራሻ ፊንፊኔ ከተማ ውስጥ ሆኖ በአዳማ-ከተማ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፬ <u>ዓላማ</u>
ጽ/ቤቱ ከዚህ በታች የተገለጹትን ዓላማዎች ይኖረዋል።
፩. በማስተር ፕላን ማሻሻያ ጥናት የአዳማ ከተማ ዕድገትና ልማት የሚመራበትን መምራትና ማዘጋጀት፣

8. Piroojektoota baajata mootummaatiin ala qoratamanii fi hojjetamaniif akkaataa maallaqni uummatarraa buusiidhaan sassaabamu ykn akkaataa gargaarsi biyya keessaa ykn biyya alaatii argamu ni qorataa, ni murteessa;
9. Gargaarsii ogeessota sadarkaa olaanaa, meeshaalee teknikaa fi ... kkf kan biraa biyya keessaa ykn biyya alaatii argamu ni qorata, yemmu argamu hojiirra akka oolu ni taassisa;
10. Hojii geggeessaa waajjirichaa ni fila, ni ramada, sababa gahiinsaatiin ykn naamusaatiin ni kaasa;
11. Mindaa hojjetootaa ni murteessa;
12. Qorannoo maastar pilaanichaa fi ijaarsi pirojektootaa yeroo xumuraman akka hojiirra oolan Mana Maree Bulchiinsa Mootummaa Naannoo Oromiyaatiif dhiyeessee ni raggaasisiisa;
13. Walumaagalatti karoora, raawwii hojii fi bu'aa waajjirichi argamisisee kaayyoo dhaabbateef waliin ni madaala;
14. Mana Maree Bulchiinsa Mootummaa Naannoo Oromiyaatiif kurmaana kurmaanaan gabaasa ni dhiyeessa.

8. *Walgahii Boordii Hordoffii fi To'annoo*

1. Walgahiin boordii kurmaanaan ni adeemsifama, haa ta'u malee yeroo walitti qabaadhaan walgahii ariifachiisaan yoo waamame, ykn miseensota saddeetii (8) oliin yoo barreefamaan gaafatame walgahuun ni danda'ama;
2. Miseensotiin %50 + tokko (1) fi kanaa ol walgahii boordiichaarratti argamnan, walgahichi adeemsifamuu ni danda'ama;
3. Haalli boordichi murtii itti dabarsu, walgahiirratti miseensota argaman keessaa sagalee caalmaadhaan yoo deggeerame ta'e, sagaleen bakka lamatti qixxee addaan qoodamnaan immoo walitti qabaan garri sagalee itti kenne murteessaa ta'a;
4. Tumaatni keewwata kanaa akkuma eegametti ta'ee, Boordiin dambii sirna walgahiisaa baafachuu ni danda'a;
5. Iddoon walgahii galma Waajjira Pireezidaantii Bulchiinsa Mootummaa Naannoo Oromiyaatti adeemsifama.

9. *Koreen Hirmaannaa Ummataa Bakka Bu'oota Qaamolee Armaan Gaditti ibsaman Miseensummaadhaan ni Qabaata*

1. Afyaa'ii Caffee Mootummaa Naannoo Oromiyaa, walitti qabaa;
2. Abbaa Gadaa Oromoo Naannoo Adaamaa ykn shawa Bahaa, miseensa;
3. Maanguddoo Mootummaa Naannootiin filatamu tokko (1) Miseensa;
4. Dhaabbata Demokraatawaa Uummata Oromoo, miseensa;
5. Waldaa Qotee Bulaa Naannoo Adaamaa, miseensa;
6. Waldaa Dubartootaa Oromiyaa, miseensa ;
7. Waldaa Dargaggootaa Oromiyaa, miseensa;
8. Waldaa Barsiosota Oromiyaa, miseensa;
9. Waldaa Gargaarsaa (NGOs) Adaamaa, miseensa;
10. Waldaa Daldaltootaa Adaamaa, miseensa;
11. Waldaa Amantii Mosilimootaa Oromiyaa, miseensa;
12. Waldaa Amantii Piroteestaantotaa Adaamaa, miseensa;
13. Waldaa Amantii Orotdoksii Adaamaa, miseensa;
14. Waldaa Hojjetoota Dafqaan Bulaa Adaamaa, miseensa;
15. Hojii Geggeessaa Waajjirichaa fi Hojii Geggeessaa Gorsituu (sagalee tokko qabachuudhaan), barreessaa.

10. *Aangoo fi Hojii Koree Hirmaannaa Uummata*

1. Kaayyoo Waajjirichaa Uummataaf ifa ni godha, hojiirrattis hirmaannaa uummataa ni kakaasa;
2. Pirojektoonni hojiin isaanii hirmaannaa uummataatiin geggeeffamanirratti uummatni, mallaqaan, humnaan, yaadaani fi gargaarsa bifa adda addaatiin akka qooda bahu ni taasisa;



፰. ከመንግሥት በጀት ውጭ ለሚጠኑ እና ለሚሰሩ ፕሮጀክቶች ገንዘብ ከሕዝብ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ ወይም ከአገር ውስጥ ወይም ከውጭ አገር ወይም ከውጭ አገር እርዳታ የሚገኝበትን ሁኔታ ያጠናል፣ ይወስናል ፡፡
፱. የከፍተኛ ደረጃ ባለሙያዎች፣ የቴክኒክ መሣሪያዎች እና እነዚህን የመሳሰሉና ሌላም እርዳታ ከአገር ውስጥ ወይም መውጭ አገር እንዲገኝ ያጠናል፣ ሲገኝ ሥራ ላይ እንዲውል ያስደርጋል፣
፲ የጽ/ቤቱን ሥራ አስኪያጅ ይመርጣል፣ ይመድባል፣ በብቃት ወይም በዲስፕሊን ምክንያት ያነሳል፣
፲፩ የሠራተኞች ደመወዝ ይወስናል፣
፲፪ የማስተር ፕላኑ ጥናትና የፕሮጀክቶች ግንባታ በሚጠናቀቁበት ጊዜ ሥራ ላይ እንዲውሉ ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት አስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል፡፡
፲፫ ባጠቃላይ እቅድ፣ የሥራ አፈፃፀምና ጽ/ቤቱ ያስገኘ ውን ውጤት ከተቋቋመለት ዓላማ ጋር ይመዝናል፡፡
፲፬ ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፰. <u>የክትትልና ቁጥጥር ቦርድ ስብሰባ</u>

፩. የቦርድ ስብሰባ በየሩብ ዓመቱ ይካሄዳል፣ ይሁን እንጂ በሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ከተጠራ፣ ወይም ከስምንት (8) በላይ አባላት በጽሁፍ ከተጠየቀ መሰብሰብ ይቻላል፡፡
፪. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ፶ በመቶ + አንድ (1) እና ከዚህ በላይ አባላት ከተገኙ ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል፡፡
፫. ቦርዱ ውሳኔ የሚያስተላልፍበት ሁኔታ በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት መካከል በድምጽ ብልጫ ከተደገፈ ሆኖ፣ ድምጽ እኩል ሁለት ቦታ ከተከፈለ ደግሞ ሰብሳቢው ድምፅ የሰጠበት ወገን ወሳኝ ይሆናል፡፡
፬. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቦርዱ የስብሰባውን ሥነ-ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡
፭. የስብሰባው ቦታ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት አዳራሽ ይካሄዳል፡፡

፱. <u>የህዝብ ተሳትፎ ኮሚቴ ከዚህ ቀጥሎ የተገለጹት አካላት ተወካዮችን በአባልነት ይይዛል፡፡</u>

፩. የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ጨፌ አፈ-ጉባኤ፣ ሰብሳቢ
፪. የአዳማ ወይም የምሥራቅ ሸዋ አካባቢ ኦሮሞ አባ ገዳ፣ አባል
፫. በክልሉ መንግሥት የሚመረጥ አንድ (፩) ሽማግሌ፣ አባል
፬. የኦሮሞ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት፣ አባል
፭. የአዳማ አካባቢ ገበሬ ማህበር ፣ አባል
፮. የኦሮሚያ ሴቶች ማህበር፣ አባል
፯. የኦሮሚያ ወጣቶች ማህበር፣ አባል
፰. የኦሮሚያ መምህራን ማህበር፣ አባል
፱. የአዳማ እርዳታ ማህበር (NGO,s) ፣ አባል
፲. የአዳማ ነጋዴዎች ማህበር፣ አባል
፲፩. የኦሮሚያ እስልምና እምነት ማህበር፣ አባል
፲፪. የአዳማ ፕሮቴስታንት እምነት ማህበር፣ አባል
፲፫. የአዳማ ኦርቶዶክስ እምነት ማህበር፣ አባል
፲፬. የአዳማ ላብ አደር ሠራተኞች ማህበር፣ አባል
፲፭. የጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅና የአማካሪ ሥራ አስኪያጅ (አንድ ድምፅ ይዘው)፣ ፀሐፊ

፲. <u>የህዝብ ተሳትፎ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩. የጽ/ቤቱን ዓላማ ለሕዝብ ግልፅ ያደርጋል፣ ለሥራም የሕዝቡን ተሳትፎ ያነሳሳል፣
፪. በህዝብ ተሳትፎ ሥራቸው በሚካሄዱት ፕሮጀክቶች ላይ ሕዝቡ በገንዘብ ፣ በጉልበት፣ በሐሳብና በልዩ ልዩ ዓይነት እርዳታ ድርሻውን እንዲወጣ ያደርጋል፣

3. Maallaqa akkaataa seera ittin walitti qabamuun herrega baankii qophaahutti ni galcha;
4. Walumaa galatti uummata bakka bu'uudhaan murtii boordiin dabarsu hojiirra ni oolchaa, yaada uummataas boordii fi Waajjirichaaf ni dhiyeessa.

11. *Walgahii Koree Hirmaannaa Uummataa*

1. Walgahiin Koree Hirmaannaa Uummataa kurmaanaan ni adeemsifama, haa ta'u malee, yeroo walitti qabaadhaan walgahii arifachiisaan yoo waamame, walgahuun ni danda'ama;
2. Miseensootiin % 50 + tokko (1) walgahii koreetirratti argamnaan, walgahiichi ademsifamuu ni dandahama;
3. Haalli koreen murtii itti dabarsu, walgahiirratti miseensota argaman keessaa sagalee caalmaadhaan yoo deggeerame ta'e, sagaleen bakka lamatti qixxee addaan qoodamnaan immoo, walitti qabaan garri sagalee itti kenne murteessaa ta'a;
4. Tumaatni keewwata kanaa akkuma eegametti ta'ee, Koreen dambii sirna walgahiisaa baafachuu ni danda'a:
5. Iddoon walgahii galma Waajjirichaatti adeemsifama.

12. Koreen Gorsaa Tekniikii Bakka Bu'oota Qaamolee Armaan Gadiitti ibsaman Miseensummaadhaan ni Qabaata
   1. Biiroo Misooma industrii fi Magaalaa Oromiyaa, Walitti qabaa;
   2. Biiroo Gamtaawina Uummataa Oromiyaa, miseensa;
   3. Koomishinii Poolisii Oromiyaa, miseensa;
   4. Waajjira Milishaa Oromiyaa, miseensa;
   5. Biiroo Maallaqaa fi Misooma Dinagdee Oromiyaa, Miseensa;
   6. Biiroo Misooma Qonnaa Oromiyaa, miseensa;
   7. Biiroo Eguumsa Naannoo Oromiyaa, miseensa;
   8. Biiroo daldalaa if Geejjibaa Oromiyaa, miseensa;
   9. Biiroo Eguumsa Fayyaa Oromiyaa, miseensa;
   10. Biiroo Qabeenya Bishaanii Oromiyaa, miseensa;
   11. Biiroo Barnootaa Oromiyaa, miseensa;
   12. Biiroo Albuudaa fi Inarjii Oromiyaa, miseensa;
   13. Biiroo Hojjetootaa fi Dhimma Hawaasummaa Oromiyaa, miseensa;
   14. Bakka Bu'aa Biiroo Dargaggootaa fi Ispoortii Oromiyaa, miseensa;
   15. Abbaa Taayitaa Daandii Baadiyyaa Oromiyaa, miseensa;
   16. Intarpiraayizii indusitrii Xixiqqaa Oromiyaa, miseensa;
   17. Korporeshinii Humna ibsaa Itoophiyaa, miseensa;
   18. Korporeshinii Telekominkeeshini Itioophiyaa, miseensa;
   19. Hojii Geggeessaa Waajjirichaa fi Hojii Geggeessaa Gorsituu (Sagalee tokko qabaachuudhaan), barreessaa.

13. *Aangoo fi Hojii Koree Gorsaa Teknikii*
Ittiwaamamni isaa Boordii Hordoffii fi To'annoo tiif ta'ee, Aangoo fi hojii armaan gadii ni qabaata:

1. Waajjirichaaf gorsa teknikki oguummaa biirooleesaanii bakka bu'uudhaan ni kenna;
2. Qulqullinaa fi sadarkaa bu'aa qorannoowwanii ni madaala;
3. Ragaalee adda addaa qorannoo pirojektootaa gabbisan biiroolee saaniirraa walitti qabuudhaan waajjirichaaf ni kenna;
4. Bu'aan qorannoo adda addaa boordiitti dhiyaachuun dura yaada irratti kennee akka darbu godha;
5. Qulqullinaa fi sadarkaa qorannoowwanii fi hojii adda addaarratti hubannoo fi madaalliisaa boordiidhaaf ni gabaasa;



፫. በህግ መሰረት የሚሰበሰበውን ገንዘብ በሚዘጋጀው የባንክ ሂሳብ ያስገባል፡፡
፬. ባጠቃላይ ሕዝቡን በመወከል ቦርዱ የሚያስተላልፈውን ውሳኔ ሥራ ላይ ያውላል፣ የህዝቡንም ሀሳብ ለቦርድና ለጽ/ ቤቱ ያቀርባል፡፡

፲፩. <u>የሕዝብ ተሳትፎ ኮሚቴ ስብሰባ</u>

፩. የህዝብ ተሳትፎ ኮሚቴ ስብሰባ በየሩብ ዓመቱ ይካሄዳል፣ ይሁን እንጂ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ በሚጠራበት ጊዜ መሰብሰብ ይቻላል፡፡
፪. በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ፶ በመቶ + አንድ (፩) አባላት ከተገኙ ስብሰባው ሊካሄድ ይቻላል፡፡
፫. ኮሚቴው ውሳኔ የሚያስተላልፍበት ሁኔታ በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት መካከል በአብላጫ ድምጽ የተደገፈ ሆኖ፣ ድምፅ እኩል ሁለት ቦታ ከተከፈለ ደግሞ ሰብሳቢው ድምፅ የሰጠበት ወገን ወሳኝ ይሆናል፡፡
፬. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኮሚቴው የስብሰባውን ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
፭. የስብሰባው ቦታ በጽ/ቤቱ አዳራሽ ይካሄዳል፡፡

፲፪. <u>የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ ከዚህ በታች የተገለጹትን አካላት በአባልነት ይኖረዋል፡፡</u>

፩. የኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ፡- ሰብሳቢ፣
፪. የኦሮሚያ ሕዝብ ማደራጃ ቢሮ፡- አባል
፫. የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ፡- አባል
፬. የኦሮሚያ ሚሊሻ ጽ/ቤት፡- አባል
፭. የኦሮሚያ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፡- አባል
፮. የኦሮሚያ ግብርና ልማት ቢሮ፡- አባል፣
፯. የኦሮሚያ የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ፡- አባል፣
፰. የኦሮሚያ ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ፡- አባል፣
፱. የኦሮሚያ ጤና ጥበቃ ቢሮ፡- አባል
፲. የኦሮሚያ ውሃ ሀብት ቢሮ፡- አባል
፲፩. የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፡- አባል
፲፪. የኦሮሚያ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ፡- አባል
፲፫. የኦሮሚያ ሠራተኞችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፡- አባል
፲፬. የኦሮሚያ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ተወካይ፡- አባል
፲፭. የኦሮሚያ ገጠር መንገድ ባለሥልጣን፡- አባል
፲፮. የኦሮሚያ ጥቃቅን ኢንዱስትሪ ኢንተርፕራይዝ፡- አባል፡፡
፲፯. የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን፣ አባል፣
፲፰. የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒሽን ኮርፖሬሽን፣ አባል፣
፲፱. የጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅና የአማካሪ ሥራ አስኪያጅ (አንድ ድምፅ ኖሯቸው)፣ ፀሐፊ

፲፫. <u>የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>

ተጠሪነቱ ለክትትልና ቁጥጥር ኮሚቴ ሆኖ፣ ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር፡፡

፩. ለጽ/ቤቱ ቢሮዎቻቸውን በመወከል ሙያዊ የቴክኒክ ምክር ይሰጣል፣
፪. የጥናቶችን ውጤት ጥራትና ደረጃ ይመዝናል፣
፫. የፕሮጀክቶችን ጥናት የሚያዳብሩ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ከየቢሮዎቻቸው በመሰብሰብ ለጽ/ቤቱ ይሰጣል፡፡
፬. የልዩ ልዩ ጥናት ውጤት ለቦርዱ ከመቅረቡ በፊት ሀሳብ ሰጥቶበት እንዲተላለፍ ያደርጋል፣
፭. የጥናቶችን ጥራትና ደረጃ እና በልዩ ልዩ ሥራ ላይ ግንዛቤውንና ምዘናውን ለቦርዱ ያቀርባል፣

6. Hojjetoonni mootummaa qorannoo fi hojiin kun isaan ilaalu akka irratti hirmaatan gochuudhaan muuxannoo argataniin dandeettiin akka guddatu ni taasisa.

14. *Walgahii Koree Gorsaa Teknikii*

a) Walgahiin Koree kanaa ji'a lama-lamaan ni adeemsifama. haata'u malee, yeroo walitti qabaadhaan algahii arifachiisaan yoo waamame walgahyuun ni danda'ama;
b) Miseensootiin %50 + tokko (1) walgahii koreerratti argamnaan, walgahiichi adeemsifamuu ni dandahama;
c) Haalli koreen murtii itti dabarsu, walgahiirratti miseensoota argaman keessaa sagalee caalmaadhaan yoo deggarame ta'e; sagaleen bakka lamatti qixxee addaan qoodamnaan immoo, walitti qabaan garri sagalee itti kenne murteessaa ta'a;
d) Tumaatni keewwata kanaa akkuma eegametti ta'ee, koreen dambii sirna walgahiisaa baafachuu ni danda'a;
e) Iddoon walgahii galma Waajjirichaatti ta'a

15. *Aangoo fi Hojii Waajjirichaa*

1. Waajjirichi aangoo fi hojii kanatti aanan ni qabaata: Maaster pilaaniin magaalattii fooyya'ee akka hojjetam uuf:
   1.1. Haala adda addaa master pilaanichi itti hojjetamuu (qoratamuu) danda'u qaamota dhimmi ilaaluu waliin mariyachuudhaan ykn qorachuudhaan murteedhaaf ni dhiheessa, haala murtaa'een akka hojii irra oolu ni taasisa;
   1.2. Hojiin fooyya'iinsa maastar pilaanichaa haala waliigaltee barbaadameen raawwatamuu isaa ni geggeessa, yeroodhaan akka irratti mari'atamu ni taasisa;
   1.3. Hojiiwwan ijaarsa magaalicha keessatti hojjetaman maastar pilaanii foyya'aa jiruun walsimuu isaanii qaamota dhimmi ilaalu qunnamuudhaan tarkaanfiin barbaachisu akka fudhatamu ni taasisa;
   1.4. Qorannoon foyya'iinsa maastar pilaanichaa qoratamee yeroo xumuramee hojiirra ooluuf qophaahu, Mana Maree Bulchiinsa Mootummaa Naannoo Oromiyaatti dhiyaatee akka ragga'u karaa boordii ni dabarsa.
2. Qophii Diizaayenii fi Ijaarsa Waajjiraalee Mootummaa, Siidaa Yaadannoo Gootota Oromoo Wareegamanii fi Giddugaleessa Aadaa Oromoo:
   2.1 Iddoowwan waajjiraaleeni fi pirojektoonni itti hojjetaman filachuudhaan akka murtaa'an ni taasisa;
   2.2 Caasaa fi walqunnamtii hojii irratti hundaa'uun haala waajjiraaleeni fi pirojektoonni itti hojjetaman qorachuudhaan murteef ni dhiheessa, haala murtaa'een diizaayeniin akka qophaahuu fi akka ijaaraman ni taasisa.
3. Bu'uraawwan misooma magaalichaa keessatti pirojektootaaf barbaachisaa ta'an kan keewwata xiqqaa kan jalatti ibsaman qaama dhimmi ilaalu waliin mari'achuun akka guuttaman taasisa:
   3.1 Daandiiwwan, riqichoota, boo'ii bishaanii fi kkf iddoo itti hojjetamuu qaban addaan baasuun haala itti guutamuu qaban ni mijeessa;
   3.2 Bishaan dhugaatii, humni ibsaa, bilbilli fi kkf naannoo magaalichi bal'atuutti akka diriiru ni hordofa;
   3.3 Rakkoon lolaa magaalicha keessatti mul'atu haala itti hiikamuu danda'u akka qoratamuu fi haala tartiibaan itti hojjetamu ni mijeessa.
   3.4 Rakkoo mana jireenyaa hojjetoota mootummaa naannoo salphisuuf:



፯. ይህ ሥራ የሚመለከታቸው የመንግሥት ሠራተኞች እንዲሳተፉበት በማድረግ በሚያገኙት ልምድ አቅም እንዲያድግ ያደርጋል።

፲፬. <u>የቴክኒክ አማካሪ ስብሰባ</u>

ሀ) የዚህ ኮሚቴ ስብሰባ በየሁለት ወሩ ይካሄዳል፣ ይሁን እንጂ በሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ በሚጠራበት ጊዜ መሰብሰብ ይቻላል፣
ለ) በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ፶ በመቶ + አንድ (፩) አባላት ከተገኙ ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል።
ሐ) ኮሚቴው ውሳኔ የሚያስተላልፍበት ሁኔታ በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት መካከል በአብዛኛው የተደገፈ ሆኖ፣ ድምፅ እኩል ሁለት ቦታ ከተከፈለ ደግሞ ሰብሳቢው ድምፅ የሰጠበት ወገን ወሳኝ ይሆናል።
መ) የዚህ አንቀፅ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኮሚቴው የስብሰባውን የሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣
ሠ) የስብሰባው ቦታ በጽ/ቤቱ አዳራሽ ይሆናል።

፲፭. <u>የጽ/ ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩. ጽ/ ቤቱ ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።
የከተማዋ ማስተር ፕላን ተሻሽሎ እንዲሠራ፡-
፩.፩ ማስተር ፕላኑ ሊሰራ (ሊጠና) የሚችልበትን ሁኔታ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ወይም በማጥናት ለውሳኔ ያቀርባል፣ በተወሰነው መሰረት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
፩.፪ የማስተር ፕላኑ ማሻሻያ ሥራ በተፈለገው ስምምነት መሰረት መፈፀሙን ይመራል፣ በየጊዜዉ ውይይት እንዲደረግበት ያደርጋል፣
፩..፫ በከተማው ውስጥ የሚሰሩ የግንባታ ሥራዎች በመሻሻል ላይ ከሚገኘው ማስተር ፕላን ጋር መጣጣማቸውን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመገናኘት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣
፩.፬ የከተማው ማስተር ፕላን ማሻሻያ ጥናት ተጠንቶ ተጠናቅቆ ሥራ ላይ ለመዋል ሲዘጋጅ ፣ ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት ቀርቦ እንዲፀድቅ በቦርድ በኩል ያስተላልፋል።

፪. የመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ የተሰው የኦሮሞ ጀግኖች መታሰቢያ ሐውልት እና የኦሮሞ ባሕል ማዕከል ዲዛይንና ግንባታ ዝግጅት፡-
፪.፩ መሥሪያ ቤቶችና ፕሮጀክቶች የሚሰሩባቸውን ሥፍራዎችን በመምረጥ እንዲወሰኑ ያደርጋል።
፪.፪ በመዋቅርና በሥራ ግንኙነት ላይ በመመስረት መሥሪያ ቤቶችና ፕሮጀክቶች የሚሠሩበትን ሁኔታ በማጥናት ለውሳኔ ያቀርባል፣
፫. በከተማው ውስጥ ለፕሮጀክቶች አስፈላጊ የሆኑትን መሠረተ ልማቶችን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሥር የተገለጹትን ጉዳይ ከሚመለከታቸው አካል ጋር በመወያየት እንዲሟሉ ያደርጋል።
፫.፩ መንገዶች፣ ድልድዮች፣ የውሃ ቦይ እና እነዚህን የመሳሰሉት መሠራት ያለባቸውን ቦታ በመለየት የሚሟላበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
፫.፪ ከተማው በሚሰፋበት አካባቢ የመጠጥ ውሃ፣ የመብራት ኃይል፣ ስልክና እነዚህን የመሳሰሉት እንዲዘረጋ ይከታተላል፣
፫.፫ በከተማው ውስጥ የሚታየው የጎርፍ ችግር ሊፈታ የሚችልበት ሁኔታ እንዲጠናና በዝርዝር የሚሠራበትን ሁኔታ ያመቻቻል።
፫.፬ የክልሉን የመንግሥት ሠራተኞች የመኖሪያ ቤት ችግር ለማቃለል፡-

3.5 Diizaayiniin manneen sadarkaa adda addaa akka qophaa'uu fi akka ijaaraman ni taasisa;

3.6 Hojjettoonni mootummaa naannoo waldaanis ta'ee dhuunfaadhaan haala lafa mana jireenyaa itti argatanii fi itti ijaarachuu danda'an qorachuudhaan akka hojii irra oolu ni taasisa;

3.7 Abootiin qabeenyaa manneen jireenyaa ijaaranii kireessuu, ykn gurguruu barbaadaniif iddoo manneen sadarkaa adda addaa itti ijaaraman qaama dhimmi ilaalu waliin qopheessuudhaan akka hirmaatan ni taasisa.

4. Baajata Waajjirichaatti hojii piroojektoota adda addaa tiif barbaachisu qopheessee ni dhiheessa; yammuu heyyamamu hojii irra ni oolcha;

5. Murtee fi qajeelfamni boordichaa qajellootti hojii irra ooluu isaanii duukaa ni bu'a; ni mirkaneessa;

6. Herregaa fi galmee pirojektichaa ni qaba; ni bulcha;

7. Galmee walgahii hojii boordii ni qaba;

8. Lakkoofsa herrega pirojektichaa keessatti maallaqni galuu qabu yeroon herreegichatti galii godhamuu isaa ni hordofa;

9. Hanga maallaqaa fi qabeenya daangeffamee aangoon kennameef irratti ajaja ni kenna;

10. Ibsa herrega pirojeektootaa qopheessuudhaan waggaa waggaadhaan boordiif ni dhiyeessa;

11. Abbaa qabeenyaa ni ta'a; waliigaltee ni mallatteessa; maqaa isaatiin ni himata ; ni mallatteessa; maqaa isaatiin ni himata ; ni himatama;

12. Boordii Hordoffii fi to'annotiif gabaasa hojii ni dhiyeessa;

13. Hojiiwwan biroo Mana Maree Bulchiinsa Mootummaa Naannoo Oromiyaatiin kennamaniif ni raawwata.

16. *Aangoo fi Hojii Hojii Geggeessaa*

1. Hojii adeemsisaan qajeelfama waliigalaa boordii irraa kennamuuf irratti hundaa'uudhaan hojii pirojektootaa ni karoorsa; ni gaggeessa; ni bulcha;

2. Keewwata kana keewwata xiqqaa (1)n osoo hindaangeeffamin hojii adeemsisaan:

2.1 Dambii kana keewwata (15) irratti aangoo fi hojii waajjirichaaf kennaman ni raawwata;

2.2 Hojjettoota Waajjirichaa ni qaxara; ni bulcha;

2.3 Baajata fi karoora hijii waggaa waajjirichaa qopheessee boordiif ni dhiyeessa; yemmuu hayyamamus hojii irra ni oolcha;

2.4 Haala baajataafi karoora hojii waajjirichaaf hayyamameetiin maallaqa bahii ni godha.

2.5 Waliigaltee seena; qaamota sadaffaa wajjin quunnamtii hunda irratti wajjiricha bakka bu'a;

2.6 Akka waaliigalaatti hojii pirojeektootaa duukaa bu'ee ni raawwachiisa;

2.7 Kurmaana kurmaanaan akkasumas yeroo barbaachise hunda gabaasa raawwii hojii qopheessee boordiif ni dhiyeessa;

2.8 Hojii boordiidhaan kennamuuf biroo ni raawwata.

3. Hojii Geggeessaan hojii waajjirichaa saffisiisuuf hanga barbaachisu aangoo fi hojii isaa keessaa hojjetoota waajjirichaatiif bakka bu'ummaadhaan dabarsuu ni danda'a;

4. Hojii Geggeessaan aangoo fi hojiisaa guutummaan gutuutti yeroo guyyaa soddoma (30) hincaalleef itti gaafatamaa hojjetu bakka buusuu ni dandaha, bakka bu'iinsa yeroo kana caaluuf yoo barbaachise, dursee boordiif dhiyaatee ragga'uu qaba.



፫.፭ የተለያዩ ደረጃ ቤቶች ዲዛይን እንዲዘጋጁና እንዲሰሩ ያደርጋል፣

፫.፮ የክልሉ የመንግሥት ሠራተኞች በማህበርም ሆነ በግል የመኖሪያ ቤት መሬት የሚያገኙበትን እና ሊሰሩበት የሚችሉበትን ሁኔታ በማጥናት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

፫.፯ የመኖሪያ ቤቶችን ሰርተው ማከራየት ወይም መሸጥ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች የተለያዩ ደረጃ ቤቶች የሚሰሩበትን ቦታ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በማዘጋጀት እንዲሳተፉ ያደርጋል።

፬. በጽ/ቤቱ ለልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች ሥራ የሚያስፈልገውን በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ሥራ ላይ ያውላል፣

፭. የቦርዱ ውሳኔና መመሪያ በሚገባ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

፮. የፕሮጀክቱን ሂሳብና መዝገብ ይይዛል፣ ያስተዳድራል።

፯. የቦርድ የሥራ ስብሰባ መዝገብ ይይዛል፣

፰. በፕሮጀክቱ የሂሳብ ቁጥር ውስጥ መግባት ያለበት ገንዘብ በጊዜ በሂሳቡ ገቢ መደረጉን ይከታተላል፣

፱. በገንዘብና በንብረት ላይ ተገድቦ እስከተሰጠው ስልጣን ትዕዛዝ ይሰጣል፣

፲. የፕሮጀክቶችን ሂሳብ መግለጫ በማዘጋጀት በያመቱ ለቦርድ ያቀርባል፣

፲፩. ባለንብረት ይሆናል፣ ውል ይፈርማል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

፲፪. የክትትልና ቁጥጥር ቦርድን የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፣

፲፫. በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

፲፮. <u>የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩. ሥራ አስኪያጁ ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ ላይ በመመስረት የፕሮጀክቶችን ሥራ ያቅዳል፣ ያካሂዳል፣ ያስተዳድራል፣

፪. ሥራ አስኪያጁ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሳይገደብ፣

፪.፩ በዚህ ደንብ አንቀጽ (፲፭) ላይ ለጽ/ቤቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፣

፪.፪ የጽ/ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

፪.፫ የጽ/ቤቱን የዓመት በጀትና የሥራ እቅድ አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል ፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣

፪.፬ ለጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ እቅድ መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

፪.፭ ውል ይዋዋላል፣ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሁሉም ግንኙነት ጽ/ ቤቱን ይወክላል፣

፪.፮ ባጠቃላይ የፕሮጀክቶችን ሥራ ተከታትሎ ያስፈጽማል፣

፪.፯ በየሩብ ዓመቱ፣ እንደዚሁም ባስፈለገበት ጊዜ ሁሉ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፣

፪.፰ ሌሎች በቦርድ የሚሰጡትን ተግባር ያከናውናል።

፫. ሥራ አስኪያጁ የጽ/ቤቱን ሥራ ለማቀላጠፍ የሚያስፈልገውን ያህል ከሥልጣኑና ተግባሩ መካከል ለጽ/ቤቱ ሠራተኞች በውክልና ማስተላለፍ ይችላል።

፬. ሥራ አስኪያጁ ሥልጣኑንና ተግባሩን ሙሉ በሙሉ ሠላሣ (፴) ቀን ለማይበልጥ ጊዜ የሚሠራ ኃላፊ መወከል ይችላል፣ ለዚህ ጊዜ የሚበልጥ ውክልና ካስፈለገ በቅድሚያ ለቦርድ ቀርቦ መጽደቅ አለበት።

17. Baajata Waajjirichaa fi Baajata Pirojektoonni ittiin Ijaaraman
   1. Baajatni Waajjirichaa Mootummaa Naannoo Oromiyaa irraa ramadama;
   2. Pirojektoota raawwachiisuuf baatatni kan argamu:
      2.1. Mootummaa irraa baajata ramadamu;
      2.2. Namoota dhuunfaa fi dhaabbattoota harjoomanu irraa;
      2.3. Gargaarsa irraa;
      2.4. Burqaawwan adda addaa irraa galii argamu ta'a.

18. *Waa'ee Odiitii fi Insipeekshinii*
   1. Herregni Waajjirichaa odiitara olaanaa Mootummaa Naannootiin kan qoratamu ta'a;
   2. Herregni Pirojektootaa odiitara alaa boordiin mogg-aasuun waggaa waggaadhaan qoratama;
   3. Herregni pirojektootaa kan qoratamu qajeelfama fi sirna qorannaa herregaa sadarkaa addunyaatti fudhatama argate irratti kan bu'uureffame ta'ee, odiitarri olaanaan Naannoo Oromiyaa fi Biiroon Maallaqa fi Misooma Dinagdee yaada irratti akka kennan godhama;
   4. Qorannaan teekniikaa waggaa waggaadhaan dhimmoota filataman irratti raawwatama.

19. *Deggersa Hojii*
Bulchiinsi Godina Addaa Adaamaa, Shawaa Bahaa fi Biiroleen Oromiyaa adda addaa ragaafi deggersa hojii barbaachisaa hunda Waajjirichaaf kennuu qaban.

20. *Dambii Haqame*
Dambiin Lakk. 25/1994 Dambii kanaan haqameera.

21. *Mirgaa fi Dirqama Darbu*
Mirgii fi dirqamni Waajjira Pirojektii Magaalaa Adaamaa fi Waajjira Pirojektii Ijaarsa Siidaa Yaadannoo Wareegamtootaa fi Giddu galeessa Aadaa Oromoodhaaf kan kenname Waajjira dambii kanaan hundaa'eef darbee jira.

22. *Yeroo Dambiin itti Ragga'u*
Dambiin kun Muddee 18 bara 1995 irraa kaassee kan ragga'u ta'a.

Juneeydii Saaddoo
Pireezidaantii Bkulchiinsa Mootummaa
Naannoo Oromiyaa

Muddee 18 bara 1995
Finfinnee



፲፯. <u>የጽ/ ቤቱ በጀትና ፕሮጀክቶች የሚሰሩበት በጀት</u>
   ፩. የጽ/ቤቱ በጀት ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ይመደባል
   ፪. ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም በጀት የሚገኘው፡-
      ፪.፩ ከመንግሥት ከሚመደበው በጀት፣
      ፪.፪ ግለሰቦችና ድርጅቶች ከሚያደርጉት አስተዋጽኦ፣
      ፪.፫ ከእርዳታ፣
      ፪.፬ ከልዩ ልዩ ምንጮች ከሚገኝ ገቢ ይሆናል።

፲፰. <u>ስለኦዲትና ኢንስፔክሽን</u>
   ፩. የጽ/ ቤቱ ሂሣብ በክልሉ መንግሥት ዋና ኦዲተር የሚመረመር ይሆናል፣
   ፪. የፕሮጀክቶች ሂሳብ ቦርዱ በሚሰይመው የውጭ ኦዲተር በያመቱ ይመረመራል ፣
   ፫. የፕሮጀክቶች ሂሳብ የሚመረመረው በዓለም አቀፍ
   - ደረጃ ተቀባይነት ባገኘ የሂሳብ ምርመራ መመሪያና ሥርዓት መሠረት ሆኖ የኦሮሚያ ክልል ዋና ኦዲተርና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አስተያየት እንዲሰጡበት ይደረጋል ፣
   ፬. የቴክኒክ ግምገማ በያመቱ በተመረጡ ጉዳዮች ላይ ይከናወናል።

፲፱. <u>የሥራ ትብብር</u>
የአዳማ ልዩ ዞን፣ የምሥራቅ ሸዋ ዞን መስተዳድር እና የተለያዩ የኦሮሚያ ቢሮዎች አስፈላጊውን መረጃና የሥራ ትብብር ሁሉ ለጽ/ቤቱ መስጠት አለባቸው።

፳. <u>የተሻረ ደንብ</u>
ደንብ ቁ. ፳፭/፲፱፻፺፬ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

፳፩. <u>የሚተላለፍ መብትና የግዴታ</u>
ለአዳማ ከተማ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና ለሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልትና የኦሮሞ ባህል ማዕከል ፕሮጀክት ግንባታ ጽ/ቤት የተሰጠው መብትና ግዴታ በዚህ ደንብ ለተቋቋመው ጽ/ቤት ተላልፏል።

፳፪. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>
ይህ ደንብ ከታህሣሥ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ጁኔይዲ ሳዶ
የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ፕሬዝዳንት
ታህሣሥ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም
ፊንፊኔ